# የቶሮንቶ ፐብሊክ ሄልዝ

# የንክኪ ልየታን በተመለከተ የተደረጉ ጊዜያዊ ለውጦች

በቶሮንቶ በታየው ከፍተኛ የኮቪድ-19 ክስተት የተነሳ፣ የቶሮንቶ ፐብሊክ ሄልዝ የንክኪ ልየታ ላይ ማድረግ ስላለብን ጥንቃቄ ጊዜያዊ ማሻሻያ አድርጓል። በከፍተኛ ደረጃ አደጋ በሚያመጡ ሁኔታዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ጥረት እያደረግን ነው። ይህም ማለት ኮቪድ-19 ያለባቸውን ሰዎች እንዲሁም በሽታውን ወደ ሌሎች በማስተላለፍ ለሌሎች ከፍተኛ አደጋ የሚፈጥሩትን ማለት ነው።

**ለጊዜው TPH የኮቪድ-19 ምርመራ ያደረጉ ሰዎችን ለሚከተሉት ጉዳይ የሚያገኝ ይሆናል፦**

- የኮቪድ-19 ምርመራ ውጤታቸው ፖዘቲቭ ስለመሆኑ ማረጋገጥ
- ምልክቶቹን መፈተሽ እንዲሁም ሲጀምሩ መወሰን
- ራሳቸውን ማግለል ስለመቻላቸው ማረጋገጥ አሊያም ለቶሮንቶ የበጎ ፈቃደኞች ማግለያ ማዕከል ማመልከት፤
- በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ የሚያደርጓቸውን ንክኪዎች በተመለከተ መመሪያዎችን መስጠት

TPH የኮቪድ-19 ምርመራ ያደረጉ ሰዎችን የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ምልክቶቹ ከመታየታቸው ከ14 ቀናት በፊት የነበሯቸውን የቅርብ ንክኪዎች ለመለየት በማሰብ ነው። የቅርብ ንክኪ ሲባል በቤት ውስጥ ባለ ማህበራዊ መሰባሰብ ለ15 ደቂቃዎች የቆየ ማንኛውም ግለሰብ  አሊያም በርካቶች በአንድ ላይ በተሰበሰቡበት የተገኘ የቤተሰብ አባል ያልሆነንም የሚጨምር ነው። ይህ መረጃ TPHን የሚጠቅመው ሲሆን 10 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ከፍተኛ አደጋ የሚያመጡ ንክኪዎችን በመለየት የንክኪ ቁጥጥር ስርዓቱን እና የሚደረገውን ክትትል የሚያግዝ ነው። TPH በኦንላይን ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ መረጃ የሚያሰባስብ ሲሆን ይህም በከተማው ሰዎች እንዴት እንደተጠቁ በማወቅ የኮቪድ-19ን ስርጭት ለመቀነስ ይረዳዋል። TPH በሆስፒታሎች የሚስተዋሉ ወረርሽኖች፣ በቤት ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ክትትል ለሚያደርጉ፣ በቤት ውስጥ ላሉ ጡረተኞች፣ መጠለያ፣ ትምህርት ቤት እና የህፃናት እንክብካቤ ቦታዎችን በተመለከተ ምርመራ እያካሄደ ምላሽ መስጠቱን ቀጠዋሏል።

በቶሮንቶ የሚታየው የኮቪድ-19 ተያዥ ሰዎች ቁጥር በቁጥጥር ስር ማዋል በሚቻልበት ደረጃ ላይ ሲመለስ፣ TPH የተለመደውን ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል የሚሰራውን ስራ የሚቀጥል ይሆናል።

ኖቬምበር 19/2020